በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል ሰባት

መምህር፦- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የወላጅ ፍቅር*

- እግዚአብሔር ከመፈጠራችን አስቀድሞ እኛን የሰው ልጆችን የወደደበት ምሳሌነቱን ትቶልናል፡፡
- ዓለሙን ሁሉ አስተካክሎ ፈጥሮ አመቻችቶ ሰጥቶናል፡፡ ሰውን መፍጠር በፈለገ ጊዜ በአርአያው በምሳሌው ፈጥሮታል፡፡ ‹‹እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡›› ***ዘፍጥ 1፡27፡፡***
- ከፈጠረውም በኋላ ፍጥረታትን እንዲገዛና እንዲነዳ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ ‹‹እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡›› ***ዘፍጥ 1፡28፡፡***
- እግዚአብሔር የማይለወጥ ፍቅሩን ሰጥቶናል፡፡ በበደልን ጊዜም እንኳ እግዚአብሔር ወዶናል፤ እስከዘላለምም ይወደናል፡፡
- አዳም በበደል ምክንያት ጸጋውን ከተገፈፈ በኋላ ስለሆነበት ቅጣትና ፍቅር እናነባለን፡፡ ‹‹እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም፡፡›› ***ዘፍጥ 3፡21፡፡***
- ቃየንም ከበደለ በኋላ እግዚአብሔር እንዴት ያለውን ፍቅሩን እንዳሳየን እናነባለን፡፡ ‹‹እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ ከፊትህም እሰወራለሁ በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል፡፡ እግዚአብሔርም እርሱን አለው፦ እንግዲህ ቃየንን የገደለ ሁሉ ሰባት እጥፍ ይበቀልበታል፡፡ እግዚአብሔርም ቃየንን ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገለት፡፡›› ***ዘፍጥ 4፡14-15፡፡***

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የወላጅ ፍቅር…*

- ከሁሉ በሚልጠውም ፍቅሩ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ‹‹አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ። ›› *ሉቃ 23፡34።*
- የሰውን ዘር ሁሉ ያለመለያየት ወዷል። ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።›› *ዮሐ 3፡16።*
- እንዲሁም ‹‹በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።›› *ማቴ 5፡45* እንደተጻፈልን።
- እግዚአብሔር የወደደውን ሰው ይገስጸው ነበር። ‹‹እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ።›› *ምሳ 3፡12።*
- በልበ አምላክ ዳዊት *መዝሙር 117፡18።* ‹‹መገሠጽስ እግዚአብሔር ገሠጻኝ ለሞት ግን አልሰጠኝም።» እንደተባለ እንደማንነታችን እግዚአብሔር ይገስጸናል።

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የወላጅ ፍቅር…*

- ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በቅዳሴዋ፣ በሰዓታቷ በአገልግሎትዋና በምስጋናዋ ሁሉ ከምስጢራትዋ ሁሉ እንዲካፈሉ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እንዲቀበሉ በማድረግ ያለ ልዩነት ለአማንያን ልጆቿ ያላትን ፍቅር ትገልጣለች፡፡
- ቤተ ክርስቲያናችን በፍቅር መንፈስ ለሰው ዘር ሁሉ ትጸልያለች፡- በምድር በሕይወት ለምንኖረውና በሞት ከዚህ ዓለም ለተለዩ፣ ለታመሙትና ለጤነኞች፣ ላሉትና መንገድ ለሚሄዱት፣ ለሚመሩትና ለሚመሩት፣ ለታሠሩት በግዞት ላሉትና ለተፈቱት፣ ላገቡትና ላላገቡት፣ ለወጣቶችና ለሽማግሎች፣ ንስሐ ለሚያሻቸው ኃጢአተኞች፣ ለወንዙ ውኃና ለምድር ፍሬ፣ ለነፋሳትና ለዝናሙ… ትጸልያለች፡፡
- ይህም ፍቅር፡ ፍቅር የሚያስፈልጋቸው ሁሉ የታቀፉበት ምሉእ የሆነ ፍጹም ፍቅር ነው፡፡
- የተወደዳችሁ ወገኖቼ! የአባትነትና የእናትነት (የወላጅ) ፍቅራችሁ ወዴት አለ? ደግነት ያለበት አባታዊ መሥዋዕትነት ያለበት የእናትነት ፍቅራችሁስ ወዴት ይገኛል? ይህ ፍቅር እግዚአብሔርና ቤተ ክርስቲያን ለእኛ ያላቸውን ፍቅር የሚመስል መሆን ይኖርበታል፡፡
- ልጆቻችንን በመውደዳችን ለነፍሳቸው የሚያስፈልጋቸውን የተመጣጠነ ምግብ (ምግበ ነፍስ - ቃለ እግዚአብሔር) እናቀርብላቸዋለን፡፡ በዚህም ፍቅር ያድጋሉ ይበለጽጋሉ፡፡
- ጤናማና የተመጣጠነ በሆነ ምግብ አማካይነት ልጆች በአካል እንደሚያድጉ ሁሉ የተመጣጠነ ፍቅር በማግኘታቸው በሥነ ልቦናቸው ተስተካክለው ያድጋሉ፡፡
- የልጆች ችሎታቸው በምንሰጣቸው ፍቅር የሚያድግ ሲሆን፡ በማነሱና በክፋታችንም የተነሳ ይቀንሳል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የወላጅ ፍቅር መገለጫ ምልክቶች*

1. በመስጠት የሚገለጥ ፍቅር

- እግዚአብሔር እንደወደደንና ፍቅሩንና በፍጥረታትም ላይ ሥልጣንን እንደሰጠን ወላጆችም መስጠትን መውደድ ይገባናል፡፡

*ራሳችንን መስጠት አለብን*

- ማንኛውንም ቁሳዊ ነገር ለልጆቻችን መስጠት ቀላል ነው፡፡ ነገር ግን ዋናው ቁምነገር (ሀብት) ራሳችንን መስጠታችን ነው፡፡ ይህም ማለት ጊዜአችንን፣ ጥረታችንን፣ ስሜታችንን፣… ነው፡፡ እነዚህ ለነፍስ የሚሰጡ ስጦታዎችና ሰውንም ለማነጽ (ለመገንባት) የሚጠቅሙ እንዲሁም ከቁሳዊ ስጦታዎች ይልቅ የተሚሉ ናቸው፡፡
- ወላጆቻቸው ገንዘብ ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት እጅግ ተጨናንቀው ፍቅርና ጊዜ እየነፈጓቸው በታላቅ ባለጠግነትና ድሎት ውስጥ የሚኖሩ ልጆች ስሜታዊ ክብካቤና ትኩረትን ከሌሎች የማያውቁአቸው እንግዶች ሰዎች መፈለጋቸው አይቀርም፡፡ የዚህም ውጤቱ ተገቢ ካልሆኑ ሰዎች ጋር ግኑኝነት ወደ መፍጠርና መንፈሳዊነታቸውንና ሕይወታቸውን ወደማጥፋት መድረስ ይሆናል፡፡

*አትረፍርፈን መስጠት አለብን*

- ትኩረታችን ለአካላቸው የሚሆን ምግብ መስጠት ላይ ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ ላይ ነው፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የወላጅ ፍቅር መገለጫ ምልክቶች*

*አትረፍርፈን መስጠት አለብን...*

- ስለ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ትውፊት፣ ሥርዓት፣ ታሪክ፣ መንፈሳዊ አገልግሎት ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበብንላቸው፡ ትእዛዛቱንና ታሪኮችን እየጠቀስን የግድ ማስተማር ይኖርብናል፡፡
- የቤት ሥራቸውን እንዲሠሩ የምንጠነቀቀውን ያህል ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ መዝሙረ ዳዊትን፣ ውዳሴ ማርያምን፣ ሰዓታቱን፣ መዝሙሩን፣ ጸሎቱን ሁሉ፣ ሽብሸባውን... እንዲያጠኑ መከታተል አለብን፡፡
- ለዚህም ሆነ ለወዲያኛው ዓለም የነፍሳቸው ምግብ ይህ መንፈሳዊው ምግብ ነውና፡፡ ለሰውነታችን (ለአካላችን) የሚሆነው ምግብ በዚህ ዓለም (በምድር) ላለው ሕይወታቸው ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነው፡፡

*መልሰን የምንቀበለው ባይኖርም መስጠት ይኖርብናል*

- ፍቅራችንን አድንቀው በጎ ምላሽ ባየሰጡንም አፍቃሪ ወላጅ በመሆን ለልጆቻችን መስጠት ይኖርብናል፡፡
- ጥፋታቸው ምንም ይሁን ምን ለልጆቻችን የምንሰጠውን ሁሉ በፍቅር መስጠት ይጠበቅብናል፡፡
- ቤተ ክርስቲያናችን ምንም ብድራትን ሳትጠብቅ ከጸጋው ግምጃ ቤትዋ እንደምትሰጠንና ተወዳጁ ጌታችን አምላካችንም በመስቀል የሰቀሉትን እንደወደዳቸው መውደድ አለብን፡፡

*ሳንጠየቅ አስቀድመን መስጠት ይኖርብናል*

- አምላካችን የሚሰጠንን ስጦታ እስክንጠይቀው ፈጽሞ የማይጠብቀንን አምላካችንን ምሳሌ በማድረግ መስጠት ይኖርብናል፡፡ ‹‹እንግዲህ፡፡ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና፡፡›› *ማቴ 6፡31-32፡፡*

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***የወላጅ ፍቅር መገለጫ ምልክቶች***

***ሳንጠየቅ አስቀድመን መስጠት ይኖርብናል...***

- ልጆቻችንን ምን ያህል እንደምንወዳቸው፣ እንደምንጠነቀቅላቸው፣ እንደምናደንቃቸውና ለፍላጎታቸውም መሟላት ያለንን ንቃት በሚገልጽ መልኩ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሳይጠይቁን አስቀድን እናድርግላቸው፡፡

***ሳንወቅስ መስጠት ይጠበቅብናል***

- ልጆቻችን ቢያጠፉም፣ የሰጠናቸውን ፍቅር የረሱ ቢመስሉም እንኳ ከመስጠት መታቀብ የለብንም፡፡ ይልቁኑ ለእነርሱ ያለንን ፍቅራችን እናስታውሳቸው ዘንድ ጨምረን እንስጣቸው፡፡

2. ***ያለመድልዎ የሚሰጥ ፍቅር***

- መጽሐፍ ቅዱስ ያለ መድልዎና ያለልዩነት (አንዱን ወደን ሌላውን ሳንጠላ) ልጆቻችንን እንወድ ዘንድ አዞናል፡፡
- ይህም ያዕቆብ ዮሴፍን ለይቶ በብዙ ኅብር ያጌጠችም ቀሚስ ሲያደርግለት ወንድሞቹ የቀኑ መሆናቸው በተገለጠበት ክፍል ተገልጾልናል፡፡ ‹‹እነርሱም በሩቅ ሳለ አዩት፥ ወደ እነርሱም ገና ሳይቀርብ ይገድሉት ዘንድ በእርሱ ላይ ተማከሩ፡፡ ... እነርሱም በሩቅ ሳለ አዩት፥ ወደ እነርሱም ገና ሳይቀርብ ይገድሉት ዘንድ በእርሱ ላይ ተማከሩ፡፡ ... የምድያም ነጋዶችም አለፉ እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጕድጓድ አወጡት ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት፡፡›› ***<u>ዘፍጥ 37፡18፣24፣28፡፡</u>***

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

2. ያለመድልዎ የሚሰጥ ፍቅር…

- ልጆቻችንን ባልተመሳሰለ መልኩ መቅረብ ቅንዓትና ኃይለኝነት እንዲገኝባቸው ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህም ልጆቹን አጥፊ፣ ዕቃዎችን የሚሰብሩ፣ የቤት እንስሳትን ሳይቀር የሚጎዱና በማኅበረሰባቸውም መካከል አስቸጋሪና በቀላሉም ከሰው የማይግባቡ ያደርጋቸዋል፡፡
- ርብቃ ከዔሳው ይልቅ ያዕቆብን ባቀረበችው ጊዜ የሚከተለውን ውጤት አምጥቷል፡-
    - ርብቃ ለዔሳው ፍላጎት፣ ሐዘንና ብኩርናውንም ስለማጣቱ ምንም የማታስብለትና ትኩረትም የማትሰጠው አስመስሏታል፡፡
    - ዔሳውም በያዕቆብ ላይ ያደረበት ሐዘን ተባብሶ ወንድሙን ለመግደል እስኪፈልግ ድረስ ቀንቶበታል፡፡
    - ይህም ርብቃ የዘራችው የአድልዎ ዘር አድጎ ያዕቆብ ይህን መራር ሕይወት ለራሱ እስኪቀምሰው አድርሶበታል፡፡
    - ይህም ያዕቆብ የወሰደው በረከት አጎቱ ላባ የፈጸመበትን ማታለል አስከትሎበታል፡፡
    - እናቱ ርብቃ ለርሱ የሰጠችው የተለየ ማበረታቻ፣ እርሱም ለዮሴፍ ያደረገው የተለየ ማበረታቻ፣ ዮሴፍ እንደሞተ አድርገው ባረዱት ጊዜ ታላቅ ሐዘን አስከትሎበታል፡፡
- ይህ ዓይነቱ አካሄድም ልጆችን ግትር ያደርጋቸዋል፡፡ ማንኛውንም የሚደረግላቸውን የሚጠቅማቸውንም ነገር ሳይቀር ለመቀበል ፈቃደኝነትን ያጣሉ፡፡ አመጸኞች፣ የማይታዘዙ፣ በፍቅር ካልሆነ ይህን ችግራቸውን ማሸነፍ የሚሳናቸው ይሆናሉ፡፡
- ልጅ ንዴቱን ወይም ስሜቱን መግለጽ ከተሳነው ሕይወቱ ይቃወሳል በራስ መተማመንንም ያጣል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

2. **ያለመድልዎ የሚሰጥ ፍቅር…**

- በዚህም የተነሳ በትምህርቱ፣ በአካሉ፣ በማኅበራዊ ሕይወቱ ሳይቀር ይደናቀፋል፡፡ ይህም ችግር የማንነቱ መገላጫ ወይም ተፈጥሮው አድርጎ ከመቁጠሩ በፊት መቅረፍ የሚቻለው የበዛ ፍቅር በመስጠት ነው፡፡
- ልዩ ማበረታቻ የሚያስፈልግ ሆኖ እንኳ ቢገኝ ለሚከተሉት ነገሮች ትኩረት እናድርግ፡-
  - ከልጃችን ፍላጎት ጥኩረት የሚሻው የቱ እንደሆነ በጥንቃቄ እንመርምር፡፡
  - ልዩ ድጋፉም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ ከሕመሙ እስኪያገግም፣ ወይም ሕጻንም ከሆነ እስኪያድግ ድረስ ብቻ፡፡
  - ልዩ ድጋፉም ሌሎች ልጆቻችን እስኪረዱት ለእነርሱ ያለንን ፍቅር እስክንጋፋ ድረስ የሚያደርስ እንዳይሆን ጥንቃቄ እናድርግ፡፡
  - ልጆች እርስ በርሳቸው እንደደጋገፉ እናበረታታቸው፡፡ ለምሳሌ ታላቅ ታናናሾችን እንዲንከባከብ፣ ጤነኞች የታመሙትን… ይህም እንደ ወላጅ ወንድምና እህቶቻቸውን ለመርዳት ያደረጉትን የምናደንቅና ላደረጉትም ምስጋና ማቅረብ የምንችል ስንሆን ብቻ የሚፈጸም መሆን አለበት፡፡
  - ልዩ ድጋፉ በሁለቱም ወላጆች በአንድ ጊዜ መፈጸም የለበትም፡፡ ለምሳሌ እናት ሕጻን ልጅዋን ስትንከባከብ አባት ደግሞ ለሌሎቹ ትኩረት ሰጥቶ መንከባከብ፣ ወይም እናት የታመመ ልጅዋን ስትንከባከብ አባት ደግሞ ጤነኞቹን መንከባከብ ይገባዋል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

3. ሳያበላሹ መውደድ ወይም ማፍቀር

- የወላጆች ልጆችን መውደድ ማንኛውንም ነገር እየሰጡ በማጥፋት፣ ሳይቆጡና ሳይገስጹ አይደለም፡፡
- ውሃ ለተክል አስፈላጊ ቢሆንም ሲበዛ ግን ያጠወልገዋል፡፡ ልክና ትክክለኛ ሚዛን የሌለው ፍቅርም የልጆቻቸችንን የወደፊት ተስፋ ያበላሻል፡፡
- ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ሕፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል፥ በበትር ብትመታው አይሞትምና፡፡በበትር ትመታዋለህ፥ ነፍሱንም ትታደጋለህ፡፡›› *ምሳ 23፡13-14፡፡* እንደተናገረው መጠናኛ ተግሳጽና ቅጣት ለልጆች ጤናማ አስተዳደግ አስፈላጊ ነው፡፡
- ‹‹እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ፡፡›› *ምሳ 3፡12፡፡* እንደተባለውም ተግሳጽም የፍቅር ምልክት ነው፡፡
- ጥፋት እንዳያጠፉ በፍቅር ልጆችን እየገሰጽን በውጤታማነታቸውም በመልካም ሥራቸው ሐሴት እናደርጋለን፡፡ ‹‹ልጅህን ቅጣ ዕረፍትንም ይሰጥሃል ለነፍስህም ተድላን ይሰጣታል፡፡›› *ምሳ 29፡17፡፡*
- ወላጆች ሆይ! ልጆችን ከመገሰጽ ቸል ማለት ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ኃላፊነት ቸል ማለት እንደሆነና ልጆቻችንን በማበላሸታችንም በእግዚአብሔር ፊት እንደምንጠየቅበት ልመክራችሁ እወዳለሁ፡፡ ይህም በካህኑ በዔሊ ሕይወት በግልጽ ተቀምጦ እናገኘዋለን፡፡ *ቀዳ ሳሙ ምዕ 2 - ምዕ 6፡፡*
- ካህኑ ዔሊ በአግባቡ ምዕመናኑን መምራትና እግዚአብሔርም ልጅ ይሰጣት ዘንድ ለነቢዩ ሳሙኤል እናት ለሐና ይጸልይላት ዘንድ ተችሎት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የጽድቅ ሕይወት በመራር ነገር ፈጽሞታል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

3. ሳያበላሹ መውደድ ወይም ማፍቀር…

- ልጆቹ አፍኒንና ፊንሐስ ሞቱ፣ ሠራዊቱ ተሸነፈ፣ ታቦተ ጽዮን ተማረከች እርሱም አንገቱ ተሰብሮ ሞተ፡፡ ቀዳ ሳሙ 4፡፡ የዚህ መራር የሕይወት ፍጻሜ ምክንያቱ ምንድር ነበር? ብለን ብንጠይቅ በተበላሹ ልጆቹ የተነሳ እግዚአብሔር ካህኑን ዔሊን መቆጣቱ ነበር፡፡
- ልጆቹ በኪዳኑ ታቦት ማደሪያ በደብተራ ኦሪት ከሴቶች ጋር ሲተኙ ካህኑ ዔሊ አልተቆጣቸውም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ እግዚአብሔር በአጸፋው ‹‹በማደሪያዬ ያቀርቡት ዘንድ ያዘዝሁትን መሥዋዕቴንና ቍርባኔን ስለ ምን ረገጣችሁ? እንድትወፍሩም የሕዝቤን የእስራኤልን ቍርባን ሁሉ መጀመሪያ በመብላታችሁ ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርህ?… ይህ በሁለቱ ልጆችህ በአፍኒንና በፊንሐስ ላይ የሚመጣ ለአንተ ምልክት ነው ሁለቱ በአንድ ቀን ይሞታሉ፡፡›› *ቀዳ ሳሙ 2፡29፣34፡፡*
- ስለዚህ ልጆቻችንን ሳናበላሻቸው፣ የሚጠቅማቸውን እንጂ የሚያበላሻቸውን ሳንሰጥ መውደድ ኃላፊነት እየተሰማቸው እንዲያድጉ ይረዳቸዋል፡፡
- የተበላሸ ልጅ የበለጠ መበላሸት፣ ትኩረት መሳብ፣ ሁሌ መታገዝን መፈለግ፣ ትኩረትን ፍለጋም አልበላም፣ የቤት ሥራም አልሠራም የሚል ይሆናል፡፡
- ብልሹ ልጅ ዘወትር ሌሎች በሱ ላይ ስላደረሱት ወይም ስለመጥፎነታቸው ይናገራል፤ ዘወትርም በቅንዓትም ይኖራል፡፡ ታናሽ ሲወለድም በሥነልቦናው ታማሚ ይሆናል፡፡
- እንዲህ ያለ ልጅ እንደዚህ ከቀጠለ ወደፊት አድጎ ቢያገባም ኃላፊነትን መሸከም የሚችል አይሆንም፤ በራሱ መተማመን የለውምና፡፡

# ይቆየን።

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org